# <u>ስህተትን ማመን ለመጪው ድል ዋስትና ነው</u>

ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ (መጋቢት 2006 ዓ. ም.)

በተደጋጋሚ ያለፈውን ያውም የደም ዋጋ የተከፈለበትን ተመክሮ በጥሞና መገምገም ይገባናል ስንል ዓላማችን ያለፈውን ጸጋ ብቻ ሳይሆን በተለይም ድክመቶችንና ስህተቶችን በማወቅ፣ ለሚካሄደው ትግል እርምትን አድርገን ድልን ለማረጋጋጥ እንችል ዘንድ ነው። ዘወትር ከድጡ ወደ ማጡ እንዳይሆን ዕጣ ክፍላችን ማለት ነው።

ከ1953 ኡ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ስህተቶች፣ በመንግስቱ ላይ መፈንቅል የሞከሩት ባለመማራቸው በህይወታቸው ዋጋ ከፈሉ፤ አምባገነኑም ሀገርን ለገንጣዮቹ አመቻችቶ ሊሰጥቻለ። ኢሕአፓንና ያን ጀግና ትውልድ የሚተቹትም ሀቅና ምርምርን ወደ ጎን የተዉ ከመሆናቸው ሌላ ስህተት ከሚሏቸው መማር አቅቷቸው ውድቀትን በራሳቸው ላይ ጋብዘው ለወያኔ ሰለባ ሆነዋል። የ1997 ኡን ሁኔታና የቀጠለውንም ያጤኗል። ስህተቶች ተደጋግመዋል፤ ድክመቶችም ቀጥለዋል። ወያኔን ማስወገድ የሚቻልባቸው ዕድሎችም አምልጠዋል። የኢሕአፓ አመራር በጥር/የካቲት 1971 አራተኛ ጠቅላላ ጉባኤውን በማድረግ ሰፊ ግምገማ አካሂዷል። ግምገማው በጽሁፍ መስፈር የለሌባቸውን ጉዳዮች በጽሁፍ ማስመሩና ሲገመግም ሌላ ስህተትን ከመፈጸም ባለመራቁ ጉዳት ቢደርስም ያደረገው ግምገማ ግን ከሞላ ጎደል ጠቃሚ ነበር። አያሌ ስህተቶችን የፈጸመው በአመራር የነበር አንድ ግለሰብ በተከተለው የተሳሳተ መንገድ ቢሆንም አመራሩ ይህንኑ ጠቅሶ ከህላፊነት ለመራቅ ሳይሞክር ራሱን ጥፋተኛ አድርጎ ወቅሷል። እንደ ተፈራው ሰነዱ ወደ ጠላቶች እጅ ገብቶ ዛሬ ወያኔ ድርጅቱን ለመወንጀል እየተጠቀመበት ነው።

በግምገማው ሰነድ መግቢያ ላይ ድርጅቱ ያሰፈረውን ሰፋ አድርገን እንጥቀስ፡

*"ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ብሶትና ዋይታ አምጦ የወለደው የበኩር ልጅ እንደመሆኑ መጠን........ ከፋሺስታዊ አመጽ ጋር ግብግብ እንዲገጥም ጽዋ ፈንታ ደርሶታል። ገና በዕድሜ ሳይበለጽግ፤ በልምድ ሳይዳብር፤ በጮርቃነቱ የተጣለበትን ይህንን ታሪካው ሓላፊነት ለመወጣት ከተፈጠረበት ከ 1964 ዓ.ም. --በተለይም ከ1966 ዓ. ም. ጀምሮ-- አዳዲስና ተለዋዋጭ ክስተቶች ሳያደናግሩት፤ ውስብስብ ሁኔታዎች ሳይቀይዱት፤ የትግሉን አውድማ ያጥለቀለቀው ህዝባዊና አብዮታዊ ሀይል፤ በሰፈነው ፋሺታዊ ጽልመት ሳይደናበር ትክክለኛውን የትግል ፈለግ ይዞ እንዲጓዝ የአጥቢያ ኮከብ ሆኖ ጳዳሉን ፈንጥቋል።*

*ኢሕአፓ በዚህች የሰባት ዓመት ዕድሜው ውስጥ፤ የቅጽበት ዕፎይታ ሳያገኝ፤ ብዙ ተመክሮዎችን አካብቶ የልጅ አዋቂ ሆኗል፤ አያሌ ቆራጥ ታጋዮችን አፍልቋል፤ የበለጸገ ድርጅታዊ የስራ ልምድ አግኝቷል፤ በሀገር*

ውስጥም በውጭ ሀገርም ታዋቂነትን አትርፏል፤ አብዮታዊ ንድፈ ሀሳብን ከግብር ጋር ለማዋሀድ ያደረገው ቅልጥፍናና ችሎታ፣ ድርጅታዊ ጥንካሬውና ትግሉን ሲጀምር የተከተለው የፖለቲካ መስመር ጥራት በሰፊው ህዝብ እንዲታቀፍ አድርጎታል። ከአንድ አፍታም ከጎኑ ሳይለይ፤ ግንባሩን ሳያጥፍ፤ በከፈለው አቻ የማይገኝለት መሥዋዕትነት የጭቁኑ ሕዝብ ጋሻ መከታነቱን አስመስክሯል። ከሁሉም በላይ፤ ለቆሙለት ትክክለኛ ዓላማ፤ ለጭቁኑ ሕዝብ ፍቅር፤ ወደር በሌለው ላባደራዊ ሞራልና ጀግንነት በትግል ሜዳ የሚወድቁ ቆራጥ ታጋዮችን በማፍራት፤ ለረጅሙ ትግል አስተማማኝ መሰረት የሚሆነው አብዮታዊ ትውልድ ታንጾ የሚወጣበትን ባህልና ገድላዊ የህይወቱን ፈለግ ሊከተልም ችሏል።

ይህም ሁሉ ሆኖ ኢሕአፓ ግን ለጋ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን ተማሪም አስተማሪም ሁኖ እየታገለና እያታገለ ትግሉን በሚመራበት ጊዜ ብዙ ድክመቶችን አሳይቷል፤ አያሌ ስህተቶችን ፈጽሟል። ኢሕአፓ ምን ዓይነት አበይት ስህተቶችን ሰራ? ምን ምን ጉልህ ድክመቶችን አሳየ ስንል፤

---የፓርቲው ትክክለኛ መስመር ተዛብቶ እንዲቀርብና ይኸው መዛባት በአንዳንድ አቅዋሞችና እርምጃዎች እንዲጸባረቁ ተደርጓል፤

- የፓርቲው ትክክለኛ መስመር ተዛብቶ እንዲቀርብና ይኸው መዛባት ተንጸባርቋል፤
- የአንዳድንድ መርሆዎች በትክክል በስራ ላይ አለመዋልን እንመለከታለን፤
- የመዋቅርን ከኀቡዕ አሰራር ጋር አለመጣጣም እንገነዘባለን፤
- የመደባዊ ይዘት ሚዛኑን ያልጠበቀ ምልመላ እንደተካሄደ እንረዳለን፤

እነሆም የፓርቲው አመራር፤ የፓርቲውን የስራ ክንውንና ሰራዊቱንም በእያንዳንዱ ዘርፍ ገምግሞ ሲያቀርብ፤ ይህ ባለፉት ዓመታት ሁኔታዎች ባለመፍቀዳቸው የዘገየ ገምገማ የሚከተሉትን ግቦች እንዲመታ የታቀደ ነው፤

- የተፈጸሙት ስህተቶችና ጥፋቶች ምን ምን እንደሆኑ/የመስመር፤ የመዋቅር፡ የአሰራር፤ የመርህና ወዘተ ነጥሎ በማውጣት፤
- ስህተቶቹንና ጥፋቶችን በማረም ዳግመኛ እንዳይሰሩ ለማድረግ፤
- ከስህተቱ ትምህርት ለመገብየት/በመገምገም፤ በመተንተን በመጭመቅ፤
- ፓርቲውን ውስጣዊ ተሃድሶ ለማቀዳጀት።

አንድ የላባደር ፓርቲ በየጊዜው ራሱ ካልገመገመ፤ የፖለቲክ መስመሩን ርቱዕነት፤ የአቋሙን ትክክለኛነት፤ የአሰራሩን ዴሞክራሲያዊነት፤ የመዋቅሩን አመቺነት፤ የመርሆቹን ተፈጻሚነት፤ የመደብ ይዘቱን ሚዛናዊነት ካልመረመረ፤ ከዚህም ተነስቶ በስህተቶቹና ድክመቶቹ ላይ በፍጹም ቆራጥነት ለመዝመት ዝግጁና ስንዱ

*ካልሆነ፤ ስህተቶቹ እያጥለቀሉት፤ ድክመቶቹ እየደፈቁት ፤ ቀስ በቀስ ላባደራዊና አብዮታዊ ጠባዮቹን እየጣለ፤ የአብዮት መሪነቱን እየለቀቀ፤ የዓመጽ ክንዱ እየዛለ፤ ከላሽ ፓርቲዎች በተቆለቆሉበት ጎዳና ማዘቅዘቅ ይጀምራል። እንዲያም ሲል የፓርቲው ውስጣዊ ዴሞክራሲያዊ ህይወት ይጠፋና የርዕዮተ ዓለም ትግሉ ውስጥ ይገባል፤ ውሁዳን የሚገኑበት፤ ብዙሃን የሚሸማቀቁበት፤ አፍላቂነት የሚታቀብበት ባጠቃላይም ፓርቲው በጭቁኖች መደባዊ ጥቅም ላይ የሚደራደርበት ሁኔታ ይፈጠራል።*

*ኢሕአፓ ሀቀኛ የላባደሩ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን ገበናውን አይሸሽግም። ለስህተቶች ጥብቅና አይቆምም። የተያያዘው የትግል ጎዳና ረጅምና ዘወርዋራ እንደመሆኑ መጠን፤ ግስጋሴው ይሰምር ዘንድ ለጉዞው ምዕራፍ እያበጀ፤ የተጓዘበትን አቀበት ቁልቁለት፤ ወለፍ ዘነፍ ያለበትን፤ የገደፈውን፣ ያከለውን፤ ያጠፋውን፣ ያለማውን በጽሞና መልሶ በመመልከት፤ አካባቢውን በማማተር ጥልቀት ያለው ምርመራ ያካሂዳል። ከዚሁም ዘንድ ስህተቶቹና ድክመቶቹን ነቅሶ አውጥቶ መነሻቸውንና ሂደታቸውን፤ የተፈጸሙባቸውን ሁኔታዎችና ያደረሱትን ጉዳቶች አጢኖ ከነዚህ ስህተቶችና ድክመቶች የሚቀሰመውን ትምህርት በአኩሪ ድሎች ካከማቸው የዳበሩ ልምዶች ጋር አቀናጅቶ ትቢያውን አራግፎ፤ እድፉን ከልቶ፤ በግለ ሂስ ጸድቶ፤ አዲስ ህይወት ነሥቶ ለሚቀጥለው የትግል ምዕራፍ በብቃት ፈርጠም ብሎ ይነሳል።”*

ይህን ያለው ኢሕአፓ ሰፋ ያለ ግምገማ አድርጎ ራሱን መውቀስ ባለበት ወቅሷል። ከዚህም ጋር መነሳት ያለበት ደግሞ ይህ አራተኛ የአመራር ጉባኤ በርካታ ስህተቶች ለማረምና ሊያስተካክል ሲነሳ በአንጻሩ ለምሳሌ የኤርትራ ግንባሮችን በጥብቅ ቢያወግዝም የመገንጠል መብት በሚለው ደረጃ ላይ ያደረገው ማስተካከል አልነበረም። ይህን መብት ማወቁ ለአንድነት ይበጃል ከሚለው ግንዛቤና ድምደማ በመነሳት ማለት ነው። በሁለተኛው ጉባኤ (ቋራ 1976 ) ግን በመርህ ደረጃ ተገቢውን እርምት አድርጎ፡

- ግንባር ቀደም ድርጅት የሚለውን ሰርዞ፤
- ጸረ ኢምፔሪያሊስት አቅዋም ያላቸው ድርጅት ብቻ የሚለውን ሰርዞ መድብለ ፓርቲ ይስፈን ብሎ አቅዋሙን ገልጿል፤
- እስከ መገንጠል የሚለውን አቅዋምም ሰርዞ ለኤርትራ የፌደሬሽንን መፍትሔ አቅርቦ ባለበት፣ ወያኔ ግን ተኝቶ የነቃ ይመስል በድንገቱ የአልባኒያ አፋኝ ስርዓትና የስታሊን አዳናቂ ሆኖ ብቅ ከማለት በተጨማሪ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ የሚያጓራበት ጊዜ ነበር።

ወደ ተነሳንበት ርዕስ ስንመለስ ዋናው ነጥብ ድርጅቶች ድክመታቸውንና ስህተታቸውን አጢነው መፍትሔ መፈለጋቸው ዋና መሆኑን ይጠቁማል። ወያኔ ለስልጣን ከበቃ በኋላ ራሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች ብዙ ስህተቶች ፈጽመዋል። ወያኔ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያዊ ሆኗል ብለውም ስህተትን የፈጸሙ ጥቂቶች አልነበሩም፡፡ ሊያብሩትና ሊተባበሩት የተሰለፉትም ሆነ ተባባሪው የሆኑትም የምንረሳቸው አይደሉም፡፡

ጠባቦች ደግሞ በወያኔ ተባባሪነት የፈረደበትን አማራን ሊያጠፉ ተሰልፈው የአሶሳ ወንጀላቸውን በበደኖና አርባጉጉ፣ በአሰቦትና ምስራቅ ወለጋ ደግመዋል። አጠፋን ተሳሳትን ሲሉ ግን እስከዛሬ አላደመጥንም። ይባስ ብሎ ጸረ አማራው ዘመቻና የዘር ማጥፋቱ ጥቃት ተጠናከሯል። ወያኔ ኢሕአፓን ወግቶ ለስልጣን ሲበቃም በማገዝ ፈንታ ልጆቼ ያሉት ነበሩ--ተሳሳትን ነበር ሲሉ ግን እስከዛሬ አልሰማናቸውም። ከነመለስና ታምራት ጋር ሲተቃቀፉ የነበሩትም፤ የወያኔ ሹመኛ የነበሩትም ተሳስተን ነበር ሲሉ ገና አልሰማንም፡፡ ይባስ ብለው ጸረ ወያኔዎችን አውጋዥ ሆነዋል። የሹም ዶሮ ሆነው ከሂስ በላይ ነን በሚል እሸ አትበሉን ለሚሉት ይህን የኢሕአፓ የአራተኛ አመራር ጠቅላላ ጉባኤ የመደምደሚያ መግለጫ እንዲያዳምጡ እንጋብዛቸዋለን።

*"የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ /ፖሊት ቢሮው ጭምር/ ያሳያቸው ድክመቶችና የፈጸማቸው ስህተቶች መላውን ኢሕአፓ በጣም እንደጎዱት የተደረጉት ግምገማዎች ግልጽ አድርገዋል። ከዚሁም ዘንድ የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ላሳያቸው ድክመቶችና ለፈጸማቸው ስህተቶች ከፍተኛ ግለ ሂስን አድርጓል። የፈጸማቸውን ስህተቶችና የነበሩትን ድክመቶች ለአባላት ሲያቀርብ፤ የ አደገቱ መድን ዋስትና፤ የጥንካሬው መሰረት፤ የአቸናፊነቱ ምልክት፤ ራሱን ትሁት ኣድርጎ የሚማር፤ የሚታረም ብቻ መሆኑን በማመንና፤ ይህ በቆራጥ ታጋዮች ደም ተሏቁጦ፤ በስጋቸው ተለስኖ፤ በአጽማቸው ተገንብቶ የቆመ የአብዮታውያን ድርጅት፤ላባአደራዊ ባህርይውን ጠብቆ......በዚህ ዘዴ የጎበጠው መስተካከል፤ የተቀረፈውን መለሰን፤ መጥፎ ልምዶችም መወገድ እንዳለባቸው በማመን ነው። አንድም ደግሞ አባላት በድርጅታቸው አብዮታዊነት ላይ ያላቸውን እምነት ለማጠናከርና በዚህ አጋጣሚ ተጠቅመው ያልታዩ የተዘለሉ ስህተቶችን እንዲጠቁሙ በማድረግ ግምገማው የዳበረና የፓርቲውን ሁለንተና የዳሰሰ እንዲሆን ስለሚያስችል ነው።"*

ተመሳሳይ ግምጋሜ ያደረገ ሌላ ድርጀት አለ? ኢሕአፓ ባደረገው ግምገማ (የዛሬ 35 ዓመት) ገንጣዮችን ሁሉ በጥላትነት ፈርጆ የተገኘ ነበር። ዛሬ ከወያኔ ጋር ሲተቃቀፉ የነበሩ፣ መለስ ብለው ከወያኔ አበረ ብለው ድርጅቱን ሊወቅሱ ሲነሱ ምንኛ ዋሾ መሆናቸውን መገንዘብ እንችላለን። ዛሬ ተቃዋሚ ነን ከሚሉት ውስጥ ስንቶቹ የወያኔ ወዳጆች፤ ተሿሚዎች እንደነበሩና እስከዛሬስ አጠፋን እንዳላሉ መቸ ረሳን? እነዚህን ግን ዛሬ ታጋይ ሀገር ወዳድ ብለን አቅፈን እንደምንጎተት የምናውቀው ነው። ይህም ወደ ዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ ያመጣናል። ቀጣይ ድክመታችንንም ይጠቁመናል። የፈጸናቸው ስህተቶች በርካታ ናችው--ማረም ሲገባን ግን ድርቅ ብለን ትክክል ነን ብለን በመቀጠላችን ትግሉን ጎድተናል። ወያኔ በኢሕአፓና በሕዝብ ሬሳ ላይ ተረማምዶ ለስልጣን በአሜሪካኖች እርዳታ ሲበቃ፣ ወጣት ተማሪዎችና እነ ኢሕአፓ ሲቃዋሙ፣ ጊዜ እንስጣቸው ብለው መደገፍ ብቻ ሳይሆን ተሿሚና አጫፋሪ ሆነው የተገኙት እስከዛሬ አጠፋን አላሉም። ሕዝብን ይቅርታ አልጠየቁም። ወያኔ በተቃዋሙትና በአማራው ሕዝብ ላይ

ሲዘምት ተባባሪ የሆኑትና ፍጅትም የፈጸሙት እስከዛሬ አጠፋን ሲሉ አለመድመጣቸው ብቻ ሳይሆን ታጋይ ተብለው ተሞካሽተው ተቀበሏቸው ስንባልም ቆይቷል። ከመለስና ታምራት ጋር ሲጨባበጡ፣ ሲደጋገፉ፣ ሲሳሳቁና ሲሳለቁብን የነበሩት አጥፍተን ነበር ሲሉ የሰማ ካለ ይንገረን እንጂ፤ ዛሬ ዋና ተቃዋሚ ነን ሲሉ፤ አድምጡ እየተባልን ነው። በቀይ ሽብር ወንጀል ስንቱን የቀጠፉትም ጻረ ወያኔ ነን ማለታቸው ላይበቃ ተመልሰው ከሽብራቸው የተረፈውን ሊያጠፉ ሲቧርቁ ሀገር ወዳድ ብለው የሚያቅፏቸውንም ታዝበናል። ያን ሀገር ኣጥፊን፣ ትውልድል ጨፍጫፊ ኮሌነልና ማፈሪያ ምክትሉንም ለቃለ መጠይቅና ለህትመት ያደረሱትንም አጠፋን ሲሉ ገና አልሰማንም። ስህተት ታቅፎ እሹሩሩ እየተባለ ነው። የህብረትን ምስረታ ያደናቀፉትና ኋላም የጎዱት አጠፋን ብለው ከስህተታቸው አልተማሩም ። የ 1997 ኡ ምርጫ መደናቀፍን በተመለከተ ከአሜሪካና እንግሊዝ ጋር ሆነው ትግሉን ያፈኑት ተሳስተን ነበር ሲሉ ለመስማት አልታደልንም። ወያኔ ለምን የህዝብን ድል ሊነጥቅ ቻለ፤ የት ላይ ተሳሳትን የሚል ግምገማ አልተደረገም። የዛሬው ወያኔ ነገ ሸሚዙን ሳይቀይር የህዝብ ጎራ ዋና ታጋይ ይባላል። ወንጀለኛ ንስሓ ሳይገባ ይታቀፋል። ታጋይ ተብሎ የታቀፈው ደርጉ መሃሙዳ ጋስ የት ደረሰ? ልደቱ ክህደቱስ? ከመለስ ተጣላን ያሉት ወያኔዎች መቸ ህዝብን ይቅርታ ጠየቁ? መቸ ወያኔስ ጋር ተጋጩ፤ ተቆራረጡ? እነ ጻድቃንና ስዬ ዛሬ የት ናቸው? ትላንት ራሳቸውን አዋቂ ምሁር፣ ዶክተር አምባሳደር ብለው ሕዝብና ትግልን የጎዱትንስ ዛሬም አዋቂ ብለን ለዲስኩርና ስብሰባ እየጠራናቸው አይደለንም? የሻዕቢያ ቅጥረኞችም ታጋይ ተብለው ለመድረክ እየበቁ አይደለም? በህሊናችንና በአንጎላችን ላይ የተኛን ብንመስል መቃወም የለብንም። ከስህተታችን መማር አልቻልንም፡፡ ስንቴ አዋጡ አምጡ ተብለንስ ታልበናል? በቃ ማለቱ ምነው ከበደን? በ 500 ዶላር አርበኛ፤ በ ግድብ ግንባታ አዋጭነት ሀገር ወዳድ ትባላላችሁ ስንባል አልተሞኘንም?

ኢሕአፓ ህልውናውንና መርሁን ጠብቆ ሊቆይ የቻለው ራሱን በየጊዜው እየገመገመ ከስህተቱ ሊማርና ሊነጻ በመጣሩ ነው። ማንም ድርጅት ስህተትን ቢፈጽም የሚጠበቅ ነው -- ከተግባር የራቁ ብቻ ናቸው ተጨባጭ ስህተት የማይፈጽሙ፤ ምንም እንኳን ከተግባር መራቃቸው ከባድ ስህተት ቢሆንም። ቅዠት ተፈርቶ ሳይተኙ አያድሩም የተባለውን ያስታውሷል። ስህተት እፈጽም ይሆን በሚል ፍርሃት ከትግል መራቅ አይገባም ። ስህተትን ግን ለማረም ቆርጦ መነሳት ይገባል። የሕዝብ ትግል ተመኩሮ ትልቅ ና ሰፊ ትምህርትን ይሰጣል። ይህን በጥሞና መመርመሩ ተገቢና ግዴታም ነው። ለምን የህብረት ጥረቶቻችን የጠብቅነውን ውጤት አላስገኙም? ወርቅ አጋጣሚዎችን መጠቀም ለምን አቃተን? ለምን ዛሬስ ቢሆን መተባበር አቃተን? ለዚህ ሁሉ መልሱ ተመክሮን ግምገማና ስህተትን አምኖ መቀበልን ይጠይቃል። ሂስ ሲቀርብ ተደፈርን፣ ተጠቃን ብሎ መቆጣትና መቀየሙ ከቀደመ፤ ስህተትን እየፈጸሙ አይኔን ግንባር ያርገው ያጠፋሁት የለም ብሎ መድረቁ አቅዋም ከሆነ፤ ከስህተት መማሩ ከከበደና ይባስ ብሎ ስህተትን

መድገሙ፣ ፈሊጥና ስልጡን ፖለቲካ ከተባለ ባለበት ዕርገጥ ሳይሆን ከድጡ ወደ ማጡ መስመጡ የግድ ይሆናል። "አላውቅም አስገድሎ አያውቅም" ይላልና የሀገራችን ሰው አላውቅም ማለትም ጳያፍ አይደለም። በተለይን ራሳቸውን የሕዝብ መሪ፤ ዓይንና ጆሮ ወዘተ የሚሉ በተቻለ ትሁት ሆነው፣ ያጠፉትን አምነውና አርመውና፣ ወደፊት ለመጓዝ ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸውል። ትግሉ ለስኬቱ ይህን ይጠይቃቸውልና። የእንዶድ ሙቀጫ የለምና፣ ራሳችንን በሂስ እና እርምት ማጠናከር ይገባናል።

ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የተቃዋሚው ጎራ አያሌ ስህተቶችን እየፈጸመ በራሱ ላይ ቀንበርን ጭኗል። ይህን መካድ አይቻልም። ጊዜውን ስንቃኝ፣ የፈጸምነውን ስህተት መረዳት እንችላለን -- ባዕዳንና ወያኔ ከፈጸሙብን ጥቃት ባልተናነሰ የራሳችን መሪ ተብዬዎች፤ ዶክተር አቃፊ፣ ኢንጂነር ነን ባዮች የፈፀሙት ስህተትና በደል ልክ የለውም። ዋናው ጥፋት ግን ስህተትን ለማረም ድፍረት ማጣቱ ነው። ሀገርና ትውልድን ያጠፋውን ፈርጣጭ ግለሰብ መድረክ ሰጥተው የሚያዳንቁ አጠፋችሁ ሲባሉ አዎ ተሳስተን ነበር ማለቱ አቅቷቸውል። ሀገርን እያጠፋ ካለው ሀያል መንግስት ስር የወደቁ ከትቢያው አንነሳ ብለው እስካሁን አሉ። ሕዝብን እንደ ዕቃ የሸጡ ሀገር ወዳድ ተብለው መድረክ እየተሰጣቸው ነው። ታዲያ የራሳችን ጠላት ራሳችን ነን ቢባል ምን ስህተት አለው?

ስህተታችን አውቀንና አምነን እንታረም!

አንታበይ፤ ትሁት የሕዝብ አገልጋይ እንሁን!!

አሁንም ቢሆን ለመታረም፤ ለማበርና ለመጠናከር ጊዜው አለን!!